# <u>የቀን እንጀራ</u>

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

*በጭንቅ በመከራ ተዘርቶ፤*

*በሰንት ውጣ ውረድ ተመርቶ፤*

*ውሃ በቋጠረ መዳፍ ተፈጭቶ፤*

*በወጉ ያልተፈጨ የተከካ፤*

*በ’ንባ ታሽቶ የቦካ፤*

*ኩፍ ያለ በደም አብሲት፤*

*ሥጋ የሆነው መጨቅጨቂት፤*

*ባጥንት ማገዶ የተጋገረ፤*

*መከራ በዝቶበት ያረረ፤*

*የቀን እንጀራ ለገሰኝ፤*

*እንካ ብሎ ሰጠኝ፤*

*የማታውን ነሰቶኝ ::*

*ቸገረኝ እንዳልተወው፤*

*አረረብኝ እንዳልበላው፤*

*የማታውን እንጀራ ሰጠኝ፤ ምነው አምላኬ ምነው ?!*

*እንዴት አርጌ ልብላው ?!*

*መራቤን እያወ’ከው፤*

*መራቤን እያወ’ከው ::*

*ሐምሌ 3 ቀን 202 ዓ.ም. (July 10/2010)*